# ስለ ዲ.ሲ. (D.C.) የኑዋሪነት ቅጽ ማረጋገጫ አዘውትሮ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## የዲ.ሲ. (D.C.) ኑዋሪነት ቅጽ የግድ መሙላት አለብኝ?

ስምዎትንና የዲ.ሲ.. (D.C.) አድራሻ የሚያሳዩ ከሚከተሉት ሰነዶች መካከል አንዱን በማቅረብ ወረዳው (District) ውስጥ የሚኖሩ መሆንዎን ማረጋገጥ ይችላሉ፦

-ህጋዊ የዲ.ሲ. (D.C.) መንጃ ፈቃድ ወይም የመንጃ ፈቃድ ያልሆነ መታወቂያ ካርድ

- ህጋዊ ኮትራት፡ የኪራይ ስምምነት፡ የኪራይ ደረሰኙ፡ ስመርስት (deed) ፡ የስምምነት ወረቀቶች፡ ወይም በወረዳው (District) ውስጥ የመኖሪያ ወለድ አገድ መግለጫ (mortgage statement)

- በወረዳው (District) ውስጥ የመኖሪያ ህጋዊ የባለቤትነት ወይም የተከራይ ዋስትና (ኢንሹራንስ) ውል (insurance policy)

- ባለፉት ስድሳ (60) ቀናት ውስጥ ለዲ.ሲ.. (D.C.) መኖሪያ የተዘጋጀ የንብረት ቀረጥ ሂሳብ (Property Tax bill)

- ባለፉት ስድሳ (60) ቀናት ውስጥ የተዘጋጀ የመገልገያ ሂሳብ (a utility bill) (ውሃ፡ ጋስ፡ ሙብራት፡ ኬብል፡ ወይም የመሬት መስመር ስልክ)

-ባለፉት ሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ የተዘጋጀ የዲ.ሲ.. (D.C.) አድራሻና ለዲ.ሲ.. (D.C.) የተያዘ ቀረጥ የሚያሳዩ የመክፈያ ጉራጅ (a pay stub)

- የዲ.ሲ.. (D.C.) መራጭ መመዝገቢያ ካርድ

ከነዚህ ውስጥ አንዱም ከሌለዎ; የዲ.ሲ. .(D.C.) መኖሪያ ቅጽ የግድ መሙላት አሉብዎ።

## የዲ.ሲ.. (D.C.) ኑዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ በወረዳው (District) ውስጥ የምኖር መሆኔን ሌላ ሰው ወይም ድርጅት እንዲያረጋግጥ ይጠይቃል፤ ይህን ቅጽ ለኔ ማን ሊሞላልኝ ይችላል?

በወረዳው (District) ውስጥ ኑዋሪ መሆንዎን ለማረጋገጥ በሌላ ሰው የሚሞላው ቅጽ ሁለት ክፍል አለው - በግለሰብ ሊሞላ የሚችልና በድርጅት ሊሞል የሚችል። <u>መሞላት የሚያስፈልገው አንዱ ማረጋገጫ ክፍል ብቻ ነው።</u>

- <u>ግለሰብ:</u> በወረዳው (District) ውስጥ መኖርዎትን የሚያውቅ ማንኛውም በዲ.ሲ. (D.C.) ውስጥ የሚኖር ሰው የቅጹን ክፍል ቢ. (section B) ሊሞላልዎትና ሊፈርም ይችልላ። ይህ መኖሪያዎን የሚጋራ ሰው (a roommate), ጎረቤት፡ አከራይ (landlord), ጉዋደኛ; ወዘተ.. ሊሆን ይችላል። ይህ ሰው በተጨማሪ ከላይ ከተዘረዘሩር ሰነዶች ስማቸውንና አድራሻ የሚያሳዩ የአንዱን ቅጅ በማቅረብ ዲ.ሲ.. (D.C.) ውስጥ መኖራቸውን የግዴታ ማረጋገጥ አለበት።
- <u>ድርጅት:</u> አገልግሎት ለእርስዎ ለሚሰጥ ለዲ.ሲ.. (D.C.) ማህበራዊ አገልግሎት ድርጅት (እንደ ጤና ጣቢያ(health clinic)፡ ምግብ ማዘጋጃ (food pantry)፡ የኢሚግሬሽን አገልግሎት ድርጅት፡ የሃይማኖት ድርጅት፡ የቤት የለሽ መጠለያ፡ ወዘተ .. ለመሳሰለ) የሚሰራ ሰው እርስዎ በወረዳው ውስጥ ይኖራሉ ብሎ ካመነ የቅጹን ክፍል ሲ. (Section C) ሊሞላልዎ ይችላል። ድርጅታዊው አረጋጋጭ የድርጅቱን ታክስ መታወቂያ (tax ID) ቁጥር የሚጠየቅ ሲሆን መረጃውን ለማረጋገጥም በ'አይኤምኤ' (IMA) ይጠራሉ።

## ይህን ቅጽ ለኔ የሚሞላልኝ ሰው ለምድን ነው የግዴታ በወረዳው (District) ውስጥ መኖራቸውን ማረጋገጥ ያለበት?

በወረዳው (District) ውስጥ ለመኖራቸው ማረጋገጫ በማቅረብ፡ የርስዎትን መኖሪያ የሚያረጋግጠው ሰው እነማን እንደሆኑና የት እንደሚኖሩ ለማረጋገጥ ሌላ ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርገዋል — "መጣራት የሚችሉ ምንጩች" (verifiable sources) እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህ ተጨማሪ እርምጃ መረጃውን የበለጠ ታማኝ ሲያደርገው ለአይኤምኤ (IMA) በፍጥነት በእርግጥም እርስዎ በወረዳው (District) ውስጥ መኖርዎን እንዲወስን ቀላል ያደርግሊታል። በወረዳው (District) ውስጥ መኖርዎን አንዴ ከወሰኑ፡ የ'አይኤምኤ' (IMA) ሰራተኞች ለጤና እንክብካቤ ጥቅሞች (health care benefits)ያቀረቡትን የትብብር (Alliance) ማመልከቻዎን ሂደት መቀጠል ይችላሉ።